# የኛ ነገር!

… ዱልዱም እርሳስ ጨብጠን፣
ያልተገሩ ቃላት አምጠን፣
እንዳክታ ተፍተን…ተፍተን…፣
በብጣሽ ሉክ ጭረን… ጭረን…፣
በኮምፒዩተር ገለባብጠን፣
ለ«ፎቶ ኮፒ ማሽን» አጉርሰን፣
ሃምሳ፣ መቶ፣ ሺህ… አባዝተን፣
እንሩጥ፣ እንሯሯጥ ወረቀት ለመበተን፡፡

ደግሞም መልካም ሥራ እንደወጠነ፣
ጀብድ ፈጽሞ እንደታመነ፣
ጥርሳችንን እናግጥ…፣
የሳቅን መስሎን እንገልፍጥ፤
እናሽሟጥ፣ እናቅራራ…፣
እንቸርችር ባዶ ጉራ፡፡

ለቁምነገር ሳንታደል፣
ሳንፈልግ ፈዋሽ ጸበል፣
እንጠንዛ፣ እንሸብት…፣
እናዝግም ለከንቱ ሞት!

**የኛ ነገር!**
እንቀደድ እንተርተር፤
ስለ ወንድ..፣ ስለ ሴት፣
ስለ ቢራ፣ ስለ ጫት፣
ስለ ሥልጣን፣ ስለ ዝና፣
ወሬ ሰፍረን በቁና…፣
በቃ ይኸው ነው ምኞታችን፣
የቀን ቅዠት የሌት ሕልማችን፤
የቢራ ጠርሙስ ስንጨብጥ…፣
ደማችን በብቅል ሲፈላ፣
እንንጨርጨር፣ እንለፍልፍ…፣
ታራራራ… ላላላላ…!

ከንቱ ወሬ አሉባልታ፣
የሃሳብ ሽብር ቱማታ፣
ወዲያ ወዲህ እናምታታ፤
ስልክ እንቀጥቅጥ ጠዋት ማታ፤
ለወሬ ድል ጉሮ-ወሸባ፣
እንለፍፍ ጡሩንባ!
እንጂ ቁም ነገር ልንፈጥር?¡
ምን በወጣን! እሱስ ይቅር¡
«የኔ - የኔ» ሩጫ፣
ግልምጫ፣ ፍጥጫ፣
ወንድም ከወንድም ተኳርፎ፣
እህት ከእህት ተላክፎ...፣
ከለከፈን ክፉ ደዌ፣ ከተጣባን እርኩስ መንፈስ፣
ሳንጠራ፣ ሳንነጻ፣ ሳንመከር፣ ሳንፈወስ፣
አምናና ሃችምና፣ ትናንት ዛሬም ነገም...
አድሮ ጥሬ፣ ታጥቦ ጭቃ፣
የኛ ነገር ይህ ነው በቃ!

ደግሞኮ አፋችንን ሞልተን፣
ለ«ኢትዮጵያ ነው»... እንላለን፤
«ጽድቁ በቀረና በቅጡ በኮነነን»፤
ሌላው ይቆየንና ለራሳችንም በበቃን፤
በምኞት ፈረስ ሳንጋልብ፣ በቁም ቅዠት ሳንሰክር፣
በዝና ሱስ ሳንጠመድ፣ በቅሌት ለእብለት ሳንገብር፣
ካበጀን እኛው ለራሳችን፣ የጠራ ንጹህ ልቦና፣
ከተመራን በሥርዓት በ«ሰውነት» ጎዳና፣
ለዚህ ከበቃን ልጆቿ፣ ለመልካም ወግ-ማዕረግ፣
የፈረደባት ኢትዮጵያ ከዚህም በላይ ከኛ አትፈልግ!
እናም፤ አንዳች ቁምነገር ሳንሰራ፣
ላንታጠብ ላንጠራ፣
ላንቃችን እስኪሰነጠቅ...፣
እስኪታይ እንጥላችን ወርዶ፣
«ኢትዮጵያ - ኢትዮጵያ...» እያልን አንደንፋ...
የቁራ ጩኸት አንጩህ በባዶ!

**የኛ ነገር!**

ቆሌ ርቆን፣ አድባር ሸሽቶን፣
ወኔ ከድቶን፣ ሃሞት ፈሶን፣
ክፋት ወርሶን፣ ፍቅር አጥሮን፣
ረጂም ምላስ ብቻ ቀርቶን፣
እንደ ሳፋ... ኳ - ኳ - ኳ - ኳ፣
እንደ ቆርኪ.... ሹዋ - ሹዋ - ሹዋ - ሹዋ...፣
ኪልልል------------- እንደ ደወል፣
ጭርርርር-------------- እንደ ቃጭል...፤

አንዳች ሳንከውን፣ በባዶ እንወጠር፣ እናለክልክ፤
ድግሷ እንዳማረላት ወይዘሮ፣
እንሽኮርመም፣ እንፍነክነክ፤
እንደ ጠገበ የጅብ መንጋ፣ እናሽካካ፣ እንታመስ፣
ዛሬም እንደ ትናንቱ፣ በወንድማችን...ሬሳ ላይ እንደንስ፤
...ቃላት እንናጠቅ፣
በሃሜት እንቧጨቅ፣
እጃችንን አውጥተን...፣
ስብሰባ ላይ ቆመን፣
«ልክ-ልኩን» ነግረን፣
ያለ-ኃጢዓቱ ኮንነን፣
ሙልጭ አርገን ሰድበን፣
ከስብሰባ አዳራሽ ዳግም እንዳይመጣ፣
ወገንን እናባር፤ ጠላትን እናብዛ፤
እየከሳን እንሂድ እንዲሁ እንደዋዛ፤
ትዕግስትን ቋጥሮ ያልሸሸውን ደግሞ...፣
በከንፈር ቆዳችን ወናፍ ቱስ-----ሰርተን፣
እናናፍስ አየሩን በሃሜት በክለን፤
እንቀጥቅጥ ራስ-ራሱን፣ እንደ ጠላት እባብ፣
በአግቦ፣ በአሽሙር፣ በሽሙጥ ዱላ እንበለው እንደብድብ።

«እሱ ነው ያውና፣ እንትን -- የእንትን አባል...
ከእንትና ጋር ያለው፣ መጣ - መጣ...» እንበል፤
የሌባ ጣታችን ወደፊት ይቀሰር፣
ዐይናችን ደም ይልበስ፣ እንበል እመር፣ ኮስተር፤

ያባት ገዳይ ሳይኖር ወይ ርስት የወረሰ፣
ወንድም- ወንድሙ ላይ ጥላቻ ያነገሠ...፣
ጠመንጃማ ቢኖረን፣ ገና ድሮ ተላልቀን...
ነበር ተገላግለን፤ «ያንንም ሕዝብ» ገላግለን::

. . .አንገታችንን ቀብረን ኖረን፣
ሁላችንም ደርሰን ፖለቲከኞች ስንሆን፣
ደግሞ አገረሸብን፣ የደም አዙሪቱ፣
ያው የተለመደው የጥንት የጠዋቱ፤
በቡድን፣ በዝምድና፣ በጎጥ ተከፋፍለን፣
የታገልን መስሎን፣ እኛው ከኛው ተቋስለን፣
እንቅልፍ አጥተን ሸር እናድራ፣
በወገን ላይ እንሳል ካራ!

ዛሬም እንደቀድሞው እንፎክር፣ እንዘምር፣
ደረቅ፣ ባዶ ቃላት እንትፋ፣ እንዘርዝር፤
ዐይናችን ደም ለብሶ እንገለማመጥ፣
ጎሪጥ እንተያይ፣ ጀርባ እንሰጣጥ፤
ዳግም እማያርመን፣ መከራ እማይመክረን፣
ታሪክ እማያስተምረን፣ ሰው ሆነን፣ «ሰው» ያልሆን!

ብቻ ወሬ እንቸርችር፣
ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ወረቀት እናባር፣
ያለ የሌለውን ጨምረን፣ ጨማምረን፣
እናውራ፣ እናስወራ፣ እንምዘዝ፣እንበትን...፣

«በሬ-ወለደ*i* » እንበል፣ «በቅሎ አረገዘች*i*...»፣
አፋችንን ከፍተን፣ ሳናፍር ሳንሰለች::
እምዬ ኢትዮጵያ ስትገዘገዝ፣ የጣር ጭንቋ ሲበዛ፣
ለጉድ የጎለተን፣ ደንዝዘን እምናይ በዋዛ - ፈዛዛ፤
ከዚያም አልፈን ቢላዋ እምንስል፣
አመቻችተን ለጠላቶቿ እምናቀብል፤

«እንዴት ኅብረት አትፈጥሩም....፣
ለምን በአንድ አትሆኑም...?!»
ብሎ ሲጮኽ ሕዝብ ነዶት፣
ያገር በደል አስቆጥቶት፣
«ኅብረት?! አዎን! ኅብረት እንዲፈጠር፣
እኔ ፊቱን፣ ቀድሞውኑ ብዬ ነበር፣
ችግሩ ያለው ከነርሱ እንጅ፣ ከኔ አይደለም፣
በበኩሌ ዝግጁ ነኝ፣ እኔ ፍጹም...»
እያልን ስንለፍፍ በፊናችን፣
ምለን ስንገዘት ሁላችን፣
አ-----------! ብለን አፋችንን ልቅ ከፍተን፣
ስናስመርቅ፣ ስናስገምት፣ ውስጠ-ባዶ ቀፎአችንን፣
ጣቶቻችን፣ አመልካቾች፣ ሌባ ጣቶች፣
ፊት-ለፊት ሲቀስሩ ወደ ሌሎች፣
ጣቶቻችን፣ ሌሎች ጣቶች፣ የቀሩቱ፣
ወደኛው ልብ ያመልክቱ!!
እርስ-በርሳችን ሳንፋቀር፣ ከራሳችን ሳንታረቅ፣
እኛነታችንን ሳናጸዳ፣ ያደፈ ዲሪቷችንን ሳናወልቅ፣
እኛ ነን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆምን ባዮች?!
ለእኩልነት፣ ለዴሞክራሲ... ታጋዮች?!
ድንቄም ታጋዮች**/** ድንቄም ዴሞክራቶች**/**
እንደለመድነው የሕዝብ ትግል ቀልባሾች!
ከሥልጣን ኮርቻ ፊጢጥ ብለን ያረረውን ዳግም ልንቆላ፣
መደናበር፣ ማደናገር፣ ሩጫ---------፣ ጥድፊያ ችኮላ!?
አንድ መሆን፣ ኅብረት መፍጠር?!
ምን በወጣን፣ «ሹመት» ሲቀር?!
**የኛ ነገር!!**

---

ይህቺ «ግንፍልተኛ» ግጥም የተጫረችው *የዛሬ 12 ዓመት ሚያዚያ 1987 ዓ.ም.* ሲሆን፣ («ሕዝባዊ ማዕበል» በምትለው የግጥም መድበል 2ኛው ዕትም ላይ ወጥታለች) በወቅቱ ለነበረው አታካች የስደት ፖለቲካ የታለመች ነበረች። ከደርዘን ዓመታት በኋላም የሰደት ፖለቲካው ከእንፉቅቅ ጉዞና ከአሉባልታ ሊላቀቅ ባለመቻሉ፣ በመገረም በድጋሚ ተሰራጨች።

ይህቺ ግጥም አሁንም እንደበፊቱ የታለመችው ለስደት ፖለቲካው ባለቤት፣ «ዲያስፖራ» እየተባለ ለሚጠራውና በአገርና በሕዝብ ስም እኩይ ተግባር ለሚያከናውነው እንጂ ለማንም አይደለም።

ጌታቸው አበራ